## ትምህርት 1

**የሰው አፈጣጠር**

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማያትንና ምድርን ከፈጠረ በኋላ ከብርሃንና ጭለማ እንዲሁም ከጠፈር አንስቶ በምድር የሚገኙ ሕያዋንና ግዑዛን ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረው ቃል በመናገር ነበር። ሰውን ሲፈጥር ግን ከሌሎች የምድር ፍጥረታት ሁሉ በተለየ ሁኔታ እንደ ሚከተለው አከበረው።

1. ሰውን ሲፈጥር ግን የተለየ ትኩረትና ጥንቃቄ በማድረግ በእጁ ጠቅላላ ሰውነቱን (ውጫዊ አካሉን) ሰራው፤ በአፍንጫው ከራሱ የሕይወት እስትንፋስ እፍ በማለት ሕያው ነፍስ አደረገው።

*ዘፍ 2፥7፣ "እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከምድር ዐፈር ወስዶ ሰውን አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ።"*

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ሌሎች ፍጥረታት በፈጠረ ጊዜ እንዳደረገው ቃል በመናገር ሳይሆን በመለኮታዊ እጁ ከምድር አፈር ወስዶ የተለያየ ተግባራት የሚያከናውኑ የሰውነት ክፍሎች በመስራት ሁሉም ለአንድ ሙሉ የሰውነት አካል ጤናማነት አገልግሎት የሚሰጡና የሚተጋገዙ አድርጎ በአንድ አካል አጣመራቸው።

2. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በራሱ አምሳል ነው።

*ዘፍ1:26-27፣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ "ሰውን በመልካችን፣ በአምሳላችን እንሥራ፤ በባሕር ዓሦች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር ሁሉ ላይ፣ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው" አለ። [27] ስለዚህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፤ በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።*

እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጠረ ማለት፡- እግዚአብሔር የሰብአዊ አካል መገለጫ የሆኑት ዕውቀት፤ ስሜት፣ ፈቃድ እንዳለው ሁሉ ሰውም እነዚህ የሰብአዊ አካል መገለጫዎች እንዲኖሩት አደረገ። ከዚህም በላይ ተሻጋጋሪ የሆኑት ባሕርያቱ ቅድስና (ፍቅር፤ ፍትሃዊነት፣ ርህራሄ፣ ትዕግስት፣ ቸርነት የመሳሰሉት) ፍጹምነት የጎደላቸው በሆኑም በሰውም ሕይወት እንዲገለጹ አደረገ።

እግዚአብሔር ስሜት አለው ማለት ቁጣ፣ ደስታ፣ ሀዘን፣ መደነቅ፣ ርህራሄ...የመሳሰሉት ያሉት መሆኑን፤ ፈቃድ አለው ማለት ደግሞ የሚፈልገው/የማይፈልገው፤ የሚመርጠው/የማይመርጠው፤ ፈቃደኛ የሚሆንበትና/የማይሆንበት ሁኔታዎች መኖራቸውን የሚያሳይ ነው።

3. እባቡን ጨምሮ በምድር ላይ በፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ እንዲጠቀምባቸውና የበላይ ሆኖ እንዲገዛቸው ሾመው።

ዘፍ 1:26፣ "... *በባሕር ዓሦች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር ሁሉ ላይ፣ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው" አለ።*

ይህን ያህል ታላቅ ስፋት ያላት ምድር በውስጧ ያሉት ማዕድናት ሁሉ፣ በባህር ውስጥ ያሉት እንስሳትና ዕጸዋት ሁሉ፤ በምድር ውጫዊ ገጽ ላይ የሚገኙ እንስሳትና ዕጸዋት ሁሉ፣ በከርሰ ምድር የሚገኙ ማዕድናት ሁሉ፣ ጸሐይና ጨረቃን ጭምር እንዲገዟቸውና እንዲ ጠቀሙባቸው ለአዳምና ለዘሩ በነጻ ሰጥቷል።

ከእነዘህ ውስጥ በምድር ላይ የሚገኙ ከ30,000 በላይ የሆኑ የዕጸዋት ዝርያዎች ለሰዎች ምግብነት እንዲውሉ የተሰጡ ናቸው። ነገር ግን ከምርታማነታቸው አናሳነት እና በገበያ ላይ ካላቸው ተፈላጊነት ከፍና ዝቅ ያሉ ከመሆኑ የተነሳ በአሁኑ ጊዜ አብዛኞቹ ዕጸዋት በብዛት ተመርተው ጥቅም ላይ እየዋሉ አይደለም።

ለሰው በምግብነት እያገለገሉ ያሉት እንስሳት ዝርያ ቁጥርም ከዕጸዋቱ ቁጥር አነስ ያለ ቢሆንም በርከት ያለ ነው። ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ለምግብነት የሚውሉ በምድር ላይ የሚገኙ እንስሳት ዝርያዎች ብዛት፡-

የአጥቢ እንስሳት ዝርያ ........14

የወፍ ዝርያዎች.........10

የዓሳ ዝርያዎች..........19

በልብ የሚሳቡ እንስሳት፣..5

ነፍሳት (ኢንሴክትስ)......5፣ ናቸው።

ከዘህም ባሻገር ንብ ማር እንደ ምታመርተው ለሰው ምግብነት የሚውሉ ማር መሰል ነገሮች የሚያመርቱ 5 ዓይነት ዝርያ ነፍሳት አሉ። ለልብስና ጫማ መስሪያነት የሚያገለግሉ የበርካታ ዕጸዋትና የእንስሳት ውጤቶች ያካተቱ ናቸው።

ይሄ ሁሉና ሌሎች እዚህ ላይ ያልተጠቀሱ ስጦታዎች ተሰጥቷቸው የነበሩት አዳምና ሄዋን ኅብረታቸው ከእግዚአብሔርን ጋር መቀጠል መቻል አለመቻሉን ወደፊት እንመለከታለን።

4. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው፣ ለሰው በምድራዊ ሕይወቱ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ሰርቶና አዘጋጅቶ ከጨረሰ መኋላ ነበር። ለካስ እግዚአብሔር ጸሐይና ጨረቃን ጨምሮ ምድር በውስጧና በውጫዊ ገጽዋ የሚገኙትን ቆጥሮ ለመጨረስ የማይቻል ነገሮች ሁሉ ፈጥሮ ያዘጋጀው ለሰው መጠቀሚያ እንዲሆኑ ነው።
5. እግዚአብሔር ከአዳምና ሄዋን ጋር መግባባት እንዲችሉ የሚነጋገሩበት ቋንቋ ማወቅ አስቻላቸው። ይህ ብቻ ሳይሆን አዳም እግዚአብሔር ለፈጠራቸው ፍጥረታት ስም አውጥቶ ያም ስም እንደዚያው ሆኖ እንዲቆይ፣ አዳምና ሄዋንን ሰፊ የማስታወስ ችሎታም እንደ ተሰጣቸው አመልካች ነው። ያ ባይሆን ኖሮ ምን ማድረግ እንዳለባቸውና እንደ ሌለባቸው፤ እንዲሁም ቃሉም ሲተላለፉ የሚያመጣባቸውን ቅጣት ባልነገራቸው፣

የበረከት ቃልም ባልተናገራቸው ነበር። ዘፍ 1፡28፣ 2፡16-17፣19፣22-23፤ 3፡8-13፣ 16-19፣ 5፡1-2።

6. እግዚአብሔር ለአዳም ምድርና መላዋን እንዲሁም በውስጥዋ ያሉት ፍጥረታት ሁሉ ፈጥሮ መስጠት ብቻ ሳይሆን በኤደን ገነት ምቹ የአትክልት ስፍራ አዘጋጅቶ በስራ ብዙ እንዳይደክም የሕይወት ዛፍን ጨምሮ ለምግብነት መልካም የሆኑና ለዓይን የሚያምሩ ተክሎች የሞሉበት የሚያስፈልገውን ሁሉ አካትቶ የያዘ ውሃ ያለው በረከት ነው የሰጠው። አዳም በዚያ ካሉት ሁሉም ለምግብነት የሚውሉ ነገሮች የሕይወት ዛፍን ጭምር እንዲጠቀም ተፈቅዶለት ክፉና ደጉን የምታሳውቀው ዛፍ ብቻ እንደይበላ ተከልክሎ ነበር። የሕይወት ዛፉ ጥቅም አዳምና ሔዋን ከነዘራቸው እየበሉት ነፍሳቸው ብቻ ሳይሆን ሰውነታቸውም ሳይሞት ለዘላለም መኖር የሚያስችል ነበር። ዘፍ 3፡22
7. አዳም ብቻውን እንዳይሆን ምቹ ረዳት እንድትሆነው ሔዋንን ፈጥሮ በመስጠት ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት በማለት ባርኳቸዋል። ዘፍ 1፡28፤
8. እግዚአብሔር ከሰጠው የተፈጥሮ ምድራዊ በረከት ለራሱ በሚመቸው ሁኔታ በሚፈልገው ቅርጽ አጠናክሮና አሰማምሮ የመስራት ችሎታ ተሰጠው። ዘፍ 2፡15

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ከፈጠራቸውና የሚያስፈልጋቸው የተለያየ በረከት ከሰጣቸው በኋላ ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ በውል ባይታወቅም ከአምላካቸው ጋር ቅድስና በተሞላው ሕብረት ያለ ኃጢአት ኖረዋል።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ይሄን ሁሉ ጠቃሚ በረከት አትረፍርፎ በመስጠት የባረካቸው ቢሆንም ይህ ያማረ ሕይወት መቀጠል የሚችለው እግዚአብሔር አዳምን አትብላ ካው ዛፍ ፍሬ ሳይበላ እስከ ቀጠለበት ጊዜ ድረስ የሚጸና ነበር። ይህ የበረከትና የሰላም ሕይወታቸው በምድር ላይ እንዳይቀጥል የሚፈታተኑ ሁለት ነገሮች ነበሩ። እነርሱም ክፉና ደጉን የምታሳውቀው ዛፍና ከተፈፈጠሩት የምድር አራዊት ሁሉ ተንኮለኛ የሆነው እባብ (ሰይጣን/አሳቹ) ነበሩ።